## ው ሣ ኔ

1. አመልካች ክርክር የተነሣበትን ቤት ለመመለስም ሆነ ውዝፍ ኪራይ ለመክፈል አይገደድም ብለናል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ያስነሣው በቀድሞው ወረዳ 20 ቀበሌ 29 የቤት ቁጥር 313 የሆነው ቤት በአ/ቁ/ 47/67 ተወርሷል አልተወረሰም የሚለውን ጭብጥ የመመርመር ስልጣን የለኝም ብሎ ክሱን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 231/1/ለ/ መሠረት ወድቅ ሲያደርገው ሲገባ አከራክሮ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ በመ/ቁ. 14806 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41668 በሚያዝያ 24 ቀን 1994 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31490

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ሴርኮ እስራኤላውያን - ጠበቃ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሣሽ በመሆን በአመልካቹ ላይ ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም ያቀረበው ክስ፣ የአሁን አመልካች ቤቴን ያለሕግ አግባብ ይዞ በመቆየቱ ከመጋቢት 9 ቀን 1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 9 ቀን 1994 ዓ.ም ላለው ጊዜ ያጣሁትን ጥቅም እና የደረሰብኝን ጉዳት ብር 363,931/ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ አንድ/ ከወጪና ኪሣራ ጋር ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያቀረበ ሲሆን ከመቃወሚያዎቹም አንዱ በአዋጅ ቁ.193/92 አንቀጽ 2/3/ መሰረት ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ቤቶች በመንግስት እጅ ለቆየበት ጊዜ ለታጣ ገቢ ክፍያ መጠየቅ ስለማይቻል ክሱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የቀረበውን መቃወሚያ ከግንዛቤ በማስገባት በሰጠው ውሣኔ ቤቱ በመንግስት እጅ የቆየው ከአዋጅ ውጭ ተወስዶ በመሆኑ አዋጅ ቁ.193/92 በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ስለዚህ ወደ ፍሬ ጉዳይ

ክርክሩ መግባት ሣያስፈልግ የተጠሪውን ክስ ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አሰምተዋል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም አመልካችን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በማከራከር መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የክፍያው ጥያቄ ከዋጅ ቁ. 193/92 አኳያ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ቢቀርብም የዚህ አይነቱ መቃወሚያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244 ስር ያልተሸፈነና የፍሬ ጉዳይ ክርክር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ እስከሰጠበት ድረስ በቁጥር 341 መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት የሚመልሰው ሆኖ አልተገኘም፣ በሌላ በኩል አመልካቹ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሣይሰጥ በዚሁ ነጥብ ላይ ተመስርቶ የሰጠው ፍርድ አመልካቹን ረቺ ቢያደረግም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ባለመስጠቱ አመልካች መስቀለኛ ይግባኝ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ሊመለከተው የሚችል ሆኖ አልተገኘም በሚል አመልካቹ አላግባብ ለበለፀገበት ብር 62,970 /ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ/ ከተለያዩ ወጪና ኪሣራ ጭምር ለተጠሪው እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካቹ ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት አመልካቹ ለዚህ ችሎት ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህም ችሎት የአመልካቹን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ካቀረባቸው የመልስ መቃወሚያዎች ውስጥ አንዱ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ ቢደረግለትም መስቀለኛ ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር በቀሪዎቹ ነጥቦች ላይ የቀረበው ክርክር ሊታይለት አይገባም የመባሉን



አግባብነት ለማጣራት ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ መዝገቡንም አግባበነት ካላቸው ህጐች አንፃር መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለቀረበበት ክስ በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ያላቸውን አምስት ነጥቦችን እና መቃወሚያዎቹ ቢታለፉ በሚል ደግሞ ለክሱ ዝርዝር መልሱን አቅርቧል፡፡ የመ/ደ/ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሣኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከተባሉት ነጥቦች አንዱን መርምሮ፣ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር መግባት ሣያስፈልግ ክሱን ውድቅ አድርጌዋልሁ በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ አመልካቹ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲል ያቀረበውን ነጥብ እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነቱ ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብ ቀሪ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮችን ሣይመረምር ክሱን ውድቅ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በማንኛውም ቀመር የክሱ ውድቅ መደረግ አመልካችን ተጠቃሚ ወይም ረቺ የሚያደርግ እንደመሆኑ አመልካቹ ቀሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች እና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮች ሊመረመሩ ይገባ ነበር ሲል ይግባኝ እንዲል የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካቹ ይግባኝ ሊጠይቅ ሲችል አልጠየቀም በሚል የአመልካች መቃወሚያ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አይደለም ለዚህ ጉዳይም አግባብነት የለውም በማለት አመልካቹ ሌሎቹን መከራከሪያዎች እንዳመነ ያህል ሌሎቹን መቃወሚያዎችና የፍሬ ነገር ክርክሮች ሣይመረመሩ ውሣኔ መስጠቱ የአመልካቹን ፍትህ የማግኘት መብት በእጅጉ የሚያጣብብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእርግጥ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበው መቃወሚያ ከፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 244 አንፃር አግባብነት የለውም ማለቱ የሚነቀፍ ባይሆንም፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ የተከተለው አካሄድ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት ሲያገኝ በሚፈፀመው አግባብ ከመሆኑ አንፃር ሌሎች በፍ/ቤቱ ያልተመረመሩ መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ መቃወሚያው በማንኛውም ምክንያት ውድቅ ሲደረግ እንደሚፈፀመው ሁሉ

በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ቀሪ መቃወሚያዎችንና መከራከሪያዎችን መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ወደ ስር ፍ/ቤት ሊመልሰው ሲገባ አመልካቹ ይግባኝ አልጠየቁምና ቀሪ መከራከራያዎቻቸው አይታዩም ሲል ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል። የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም ሲል ይግባኙን መሰረዙ በተመሣሣይ ሁኔታ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው።

**ው ሣ ኔ**

1) የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39329 ሚያዝያ 14 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ብይን ውድቅ መደረጉን ተገንዝቦ የቀሩትን መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ይመለስለት ብለናል።
2) የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40110 በግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
3) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27255 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።
4) ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 31547

መጋቢት 07 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በትግራይ ክልል ደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የአሁን አመልካችን ጨምሮ በ7 ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የሟች አባታችንና የባለቤታቸው የወ/ሮ ሮማን ቢሆን የሆነውን በመቀሌ ከተማ የሚገኘውን ቤት ከ1-6 የተጠቀሱት ተከሳሾች ያለእኔ ፈቃድ ለ7ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ የሸጡ ስለሆነ ከሽያጩ ገንዘብ የእኔ ድርሻ ብር 9,375 ስለሚሆን ይህንኑ ገንዘብ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አሁን በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉት የሥር ከ1-6 ተከሳሾች ቀርበው የይርጋ ክርክር ያነሱ ሲሆን የአሁን አመልካችም ቀርበው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በሕጋዊ መንገድ እንደገዙትና ውሉም በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተመዘገበ መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የወረዳው ፍ/ቤት የሽያጩ ውል በሚመለከተው አካል መጽደቁን የቀረበው ማስረጃ የሚያረጋግጥ ከመሆኑን በላይ የተሸጠውም በብር 30 ሺ.ህ እንደሆነ መገንዘብ ስለተቻለ ከዚህ ላይ የሟች ድርሻ ብር 15 ሺ.ህ ስለሆነና ይህም